☆ ዴሞክራሲያ ☆

☆

*************☆*********

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን*

************************

## ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ለምን?

ከዴሞክራሲ መሠረታዊ ዓላማዎችና መተከላዊ መርኅዎች አንዱ፥ በሕዝብ ቀጥተኛና ነፃ ተሳትፎ ርቱዕ ምርጫ ማካሄድ ነው ። ገደብ የለሽ ነፃነቱን አረጋግጦ፥ በማንም ተፅዕኖ ሳይደረግበት ሆነ መመሪያ ሳይሰጠው ሕዝቡ በራሱ ፈቃድና ፍላጎት እንደ አሻው የፈለገውን የሚመርጥበት ዕድል ማግኘቱ፥ ለምርጫው ዉጤት ማማርና መሳካት ዋስትና እንደሚሆን የሚያከራክር ሊሆን አይችልም። ከሁሉ በፊት፥ ስለምርጫ ሲታሰብ፥ ለምርጫ የሚያስፈልጉትን ቅድመ-ዝግጅትና ከማንም ከምንም ነፃ የሆኑ ሁኔታዎችን መፍጠር ዓይነተኛና መሰረታዊ ጉዳይ ነው። በማነኛውም ሕይወት ውስጥ እንደሚከሰተው፥ ለመምረጥ፥ የሚመረጡት በዓይነትም ሆነ በብዛት በርክተው እንዲገኙ-እንዲቀርቡ የግድ ይላል ። በዓይነትም ይሁን በጥራትና በብዛት የተለያዩ ተመራጮች ለውድድር መቅረብ የተመራጮች ብቻ ሳይሆን፥ የመራጩ ሕዝብም መሠረታዊ መብት መሆኑን ያላገናዘበ ምርጫ የልጆች ጨዋታ ከመሆን አያልፍም። ከዝ ጆሮ ቆንጆ ምን ይመራርጧል ከመባሉ አስቀድሞ፥ በዓይነት፥ በጥራትና በብዛት የሚቀርቡለት ምርጫዎች፥ ለመራጩ ሕዝብ ያሻውን-የፈቀደውን ሁሉ ገላውን ሰድዶ እንዲመርጥ ዕድሉ ሰፊ ይሆናል። በተለይማ ስለሀገራዊ ምርጫ ሲታሰብ፥ መጀመሪያ ሊጠየቅ የሚገባው፥ መራጩ ማን ነው? ተመራጩስ ማን ነው ? የሚለው ሳይሆን፥ የምርጫው ሕግ፥ ደንብ፥ ሂደትና አፈፃፀሙ በማን ቁጥጥር ስር መሆን አለበት? የሚለው መሠረታዊ ኃሳብ፥ትክክለኛ መልስ ማግኘቱ ይሆናል። ይህ ጉዳይ ተገቢውን ምላሽ ሳያገኝ፥ምርጫ ብሎ ነገር የጨረባ ተስካር ማውጣት ነው። ለዚህም ነው የሚቀጥለው ምርጫ አስመልክቶ ምርጫው መካሄዱ ሳይሆን፥ምን ዓይነት ምርጫ ነው መካሄድ ያለበት የሚለው ጥያቄ ዐቢይና ወሳኝ የሚሆነው።

የአንድን ሀገር ሕዝብ መሠረታዊ መብቶችና የወደፊት ዕድል፥ በዘለቄታ መልኩ ሊወሰን የሚችለው፥ ማረጋገጫም የሚሰጠው፥ በዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ላይ የተመሠረተ ምርጫ ማካሄድ ስለሆነ፥ ይህ ዐቢይ ብሔራዊ ጉዳይ፥ ሁሉንም የሀገሪቷን ዜጋ በቀጥታ የሚመለከት እንጅ፥የአንድ ብሔር ተወካይና፥ የጥቂት ምርጥ ቡድኖች ሥራ ሊሆን አይችልም። ብሔራዊ ምርጫ ለአንድ ሀገር ሕዝብ ለሁለንተናዊ ህይወቱ መሠረት ነው። ስለሆነም፥የአንድ የምርጫ ወቅት ሊያልፍብን ነው በሚል ጉጉት፥ የምርጫ መሠረታዊ ሕጎችም ሆኑ ሥነሥርዓት ሳይረጋገጡና ሁኔታዎችና ቅድመ-ዝግጅቶች ሳይሟሉ፥ ለምርጫ ሽር-ጉድ ማለት፥ የሀገሪቱን ዜጎች መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች መጣስ ብቻ ሳይሆን፥ በራሱ በዴሞክራሲ መተከላዊ መርኅ ላይ መቀለድም ይሆናል። የሕዝብ መብት መስፈኑ በምርጫ መካሄድ ብቻ የሚገለፅ ባይሆንም፥ ፍትሐዊ ምርጫ ለማካሄድ ዴሞክራሲያዊ መብቶች፥ በተለይም ነፃ ምርጫን በተመለከተ ዕውን መሆን ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው ።

ማነኛቸውም ምርጫዎች ዓላማ ማድረግ ያለባቸው÷የዜጎች መሠረታዊ መብቶች መጠበቅ አለመጠበቃቸውን በማረጋገጡ ላይ ነው እንጅ÷ መጭው ምርጫ በምንም ዓይነትና ሁኔታ መተላለፍ የለበትም/አለበት በሚለው ላይ አይደለም ። ለይሰሙላ ምርጫ አካሂደን ነበር የሚለው ዝባ-ዝ ኪ÷ ጫና የሚሰጠው÷ለሁለት ምክንያቶች ነው ። አንደኛው÷ የውጭ ታዛቢዎችን ዕይታ ለመበረዝ ለማምታታት÷ ብሎም ከእነርሱም የሚገኘውን ምፅዋዕት እንዳይቋረጥ ለማድረግ ሲሆን÷ሁለተኛው ደግሞ ሕዝቡን የፕሮፓጋንዳቸው ሰለባ አድርገው ለሀገሪቷ የውስጥ ፖሊቲካ ፍጆታ ይጠቅመናል የሚሉትን ምኞት ለማሳካት የሚደረግ ከንቱ ሙከራ ነው ። ሁለቱም ከንቱ ውዳሴዎችና በሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚደረጉ መፈራገጦች ናቸው። የሀገሪቱን መሠረታዊ ችግሮችም ይሁን÷ የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ አይመልሱም ። አሁን ያለው የወያኔ የምርጫ ሕግና የምርጫው አስፈፃሚ ቦርድ ምርጫውን ነፃና ፍትሐዊ ለማድረግ ሳያበቁ÷ አሁንም በዚያው በአሮጌ ፈረስ መጋለብ÷ ውሀ- ቅዳ ውሀ-መልስ ነው ።

ከላይ፤ ከመጀመሪያው፤ ከዋናውና ከመሠረቱ ከደፈረሰ ከታች አይጠራም። በዚህ በተጭበረበረ ምርጫ ወያኔ አሸናፊ ነኝ ብሎ ቢያቅራራ÷ ከቶስ ይህ ለምን ይሆናል ማለት ደግሞ ÷ በኋላ በፈርስ ላይ እንደማጓጎር ይቆጠራል ። ታዲያ ይህን ከተረዳን÷ እንዲሁም የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች በገሀድ እንደሚያስረዱትም÷ መጭው ምርጫ ነፃና ርቱዕ ይሆናል ብሎ መመኘት ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ እንደማለት ነው።

አንድ ታታሪ ገበሬ የጠበቀውን ምርት ለማምረት ሲፈልግ÷ ዘር ከመዝራቱ አስቀድሞ ማሳውን አለስልሶ ማረስ እንዳለበት ሁሉ÷ በአንድ ሀገር ውስጥ ሊከናወን የሚገባውን ማነኛውንም ምርጫ የተሳካ ነበር ለማለት የሚቻለው÷ ከምርጫው በፊት የሚከናወኑት ሁለንተናዊ ዝግጅቶች ሁሉ ተሟልተው ተገኝተው ከነበረ ነው። ከሁሉ አስቀድሞ÷ በሀገሪቱ ውስጥ ያልተገደበ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሰፍኖ መገኘት አለበት። የነዋሪዎቹም ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለመረጋገጣቸው በተግባር የሚተረጎም ዋስትና ማግኘት እንዳለባቸው የግድ ይላል ። እነኝህ መሠረታዊ-ብሔራዊ ጉዳዮች ከተረጋገጡ በኋላ ነው÷ ለምርጫ ዝግጅት መነጋገር የሚቻለው። ከዚያ በኋላ የሚደረጉት የምርጫ ሂደቶችና አፈፃፀማቸው÷ ብሎም በየእርከኑ የሚደረጉ የምርጫ ክንዋኔዎችም ሆኑ ተሳትፎዎች ሳንካ እንዳይገጥማቸው ሕዝቡ እራሱ ነቅቶ ለመጠበቅ የሚኖረው ዕድል ከፍተኛ ይሆናል ። ያለ ዜጎች ሙሉና ንቁ ተሳትፎ÷ ስለምርጫ ማውራት ከንቱ ነው። የሀገሪቱን ዜጎች የ ቃተ-ኅሊና ደረጃና ብስለት÷ ከእንግዲህ ወዲህ ዝቅ አድርጎ መገመት÷ ትርፉ ራስን ማዋረድ ይሆናል። የሀገሪቱን ዜጎች ከመነሻው÷ ሂደቱና እስከ ምርጫው አፈፃፀም ድረስ÷ በተሟላ መልኩ እንዲሳተፉ ማድረግ÷ የዲሞክራሲ መሠረታዊና ዓይነተኛ መርኀ ነው።

ስለ ብሔራዊ ምርጫ ሲታሰብ÷ ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች ተሟልተው መገኘታቸውን ማረጋገጥ አማራጭ ሊኖረው አይችልም ። የመጀመሪያው ያው የተሟሉ ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ጉዳይ ሲሆን÷ ሁለተኛው ደግሞ የምርጫውን ሕግ÷ ደንብና ሥነሥርዓት ሁሉም ወገን አክብሮ የመገኘቱ ሁኔታ ነው። ሦስተኛው ደግሞ የምርጫው አስፈፃሚ አካል ነፃና ገለልተኛ መሆኑን ማረጋገጥ ይሆናል ። እነኝህ ጉዳዮች ከገዥው ፓርቲም ይሆን ከሌላ ኃይል ቁጥጥር ነፃ መሆናቸውን ሕዝቡ ማረጋገጥ የሚችልበትን ሥርዓት ማዘጋጀት አለበት ። ከዚህም በስተቀር÷ የመገናኛ ብዙኃንን በእኩል የመጠቀምና ሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ለምርጫ የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ወጭ በእኩል የማግኘት መብታቸው ሊከበርላቸው ይገባል ። የተወዳዳሪዎቹም ከቦታ ወደቦታ በነፃና ያለአንዳች ተፅዕኖ የመንቀሳቀስ÷ ሕዝብን የመቀስቀስና የማደረጀት መብት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ሊሆን ከቶ አይችልም ። የሀገር ውስጥም ይሁኑ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች በገለልተኛነት ታዛቢ የሚሆኑበትን ሁኔታ መፍጠርም የሚያከራክር አይሆንም።

ምርጫው ተጀምሮ እስከሚፈፀምበት ድረስ በሂደቱ÷ መራጩን ሕዝብ ማዋከብ÷ የምርጫ ሳጥኖችን እየከፈቱ ወደ ራስ ሳጥን መገልበጥ÷ ተራ ማጭበርበርና ማወናበድ ወዘተ.

የመሳሰሉ ቅሌቶችና ሸፍጦች ከተከሰቱ፥ ነፃ ጋዜጠኞችና የመገናኛ ብዙኃን እየተከታተሉ የማጋለጥና ለሕዝቡ የማሳወቅ ተግባራቸውን ያለስጋት የሚያከናውኑበት ሥርዓትም ሊሰናዳ ይገባል። ከእነርሱም ድፍረትና ሚዛ ዊነት እንዲኖራቸው ይጠበቃል ። በሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ፥ እንዲያው ሁሉ በእጄ ሁሉ በደጄ ከሚል ትዕቢት በመነሳት፥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ፥ በምርጫው ላይ ማነኛውንም ዓይነት፥ ተፅዕኖ እንዳያደርግ አስፈላጊውን የመቆጣጠሪያ ደንብና ሥርዓት ማበጀት፥ የምርጫው ውጤት ትክክለኛ እንዲሆን ከሚያደርጉት ማረጋገጫዎች አንዱ ይሆናል። ወያኔ ለአለፉት ሁለት ምርጫ ተብየ የወያኔ ቲያትሮች ሲያደርገው እንደነበረው፥ ምርጫን ያህል ታላቅ ብሔራዊ ጉዳይ፥ ምልዓተ-ሕዝብን ያገለለ ሊሆን ከቶ አይቻልም ። አሁንም እንደለመደው፥ ወያኔ የመጭውን ምርጫ ውጤት በቅድሚያ የሚያውቅበትንና እራሱን በአሸናፊነት ለመሰየም

የሚያስችለውን ቅድመ ዝግጅት ሁሉ በማድረግ ላይ እንደሆነ፥ ለመላው የኢትየጵያ ሕዝብ የተሰወረ ባይሆንም፥ ተቀዋሚ ድርጅቶች ይህንን መሰሪነትና ውንብድና እያዩ በአርምሞ እንዳያልፉት ሕዝብ በአንክሮ ይጠብቃቸዋል። ተገቢው ለውጥ ሳይደረግ የምርጫው ተካፋይ ለመሆን የወሰኑ ድርጅቶች ካሉ፤ የወያኔ ውንብድና ሰለባ ከመሆን ተቆጥበው፥ በኢትዮጵያ ነፃ፥ ርቱዕና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሚከሰትበትን ሁኔታ ለመፍጠር ከሚታገሉት ጎን ቆመው መታገል ይኖርባቸዋል። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የሀገራቸውን ዘላቂ ጥቅም፥ ዛሬ በሚከናወን የተጭበረበረ ምርጫ በመካፈል በሚገኝ ጥቂት የይስሙላ የወያኔ ተቀጥላ ፓርላማ መቀመጫዎች ሊለውጡት አይጠበቅባቸውም። የማነኛውም ታጋይ ድርጅት ዓላማ፥ ብኩርናን በጭብጥ ምስር መለወጥን የሚጨምር እንዳልሆነ ሕዝቡ ደህና አድርጎ ይረዳዋል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አበክሮ እንደሚያምንበት ከሆነ ደግሞ፥ተቃዋሚ ድርጅቶችን የሚመለከታቸው፥ ሀገራቸውን ከወያኔ የዘር ፖሊቲካና የአምባገነን አገዛዝ ፈልቅቀው እንዲያወጡለት ነው ። የእነርሱም ሀገራዊ ተልዕኮ ይኸ መሆን እንደሚገባው መታወቅ አለበት ።

ምርጫን አስመልክቶ፥ በኢሕአፓና በወያኔ መካከል ያለው ልዩነት፥ ልክ እንደሌሎቹ የሀገራችን መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ እንዳለው ልዩነት፥ የሰማይና የምድር ያህል ይራራቃል። እኛ ምርጫን የምናየው ከኢትዮጵያ ሀገራችን የዘለቄታና ስትራተጂያዊ ራዕይ፥ እንዲሁም ከሕዝባችን መሠረታዊና ዘለዓለማዊ ጥቅም አኳያ ነው። ይህን የረዥም ጊዜ ራዕያችንን፥ ዛሬ እንደ ዕንጉዳይ ፈልቶ፥ በማግስቱ በሚረግፍ ጊዚያዊ ፍርፋሬ ለመለወጥ ከቶ እንደማይቻለን ደግሞ በዘመነ ወያኔ ብቻ ሳይሆን፥ ባለፉትም ሥርዓቶች ያስመሰከርነው ነው። በመሠረቱ የሥልጣኑ ሁሉ ምንጭ እራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ስንል፥ መፈክር ለይስሙላ ለማሰማት ወይም ሕዝብን ለመሸንገል ሳይሆን፥ በፅኑ ከልብ አምነንበት ነው። እንዲያውም የትግላችን አልፋና ኦሜጋ ይኸው ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት የማድረጉ ተልዕኮ ነው። ዓላማችንም ሆነ ትግላችን የሚሽከረከረው፥ በሕዝባችን ነፃነትና ሉዓላዊነት፥ በሀገራችን ህልውናና በዜጎቿ እኩልነት ዙሪያ ነው ። የሀገራችን መሠረታዊና ውስብስብ ችግሮች ለአንዴና ለሁሌም እስካልተፈቱ ድረስ፥ የሕዝባችን ሁለንተናዊ መከራና ፀገም ይፈታል ብለን እራሳችንን ለማታለል እንቸገራለን ። ከሁሉ በፊት ቅድሚያ የምንሰጠው የሀገራችንን የዘለቄታ ችግር ሊፈቱ በሚችሉ የመሠረት ድንጋይና የማዕዘን አዕማድ ላይ ነው ። እነርሱም፥ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች እንዲሆም የሕግ የበላይነትና የሕዘቡ ልዕዋላዊነት ናቸው። ከሁሉ አስቀድሞ እነኝህ አዕማድ በዘለዓለማዊ መልካቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ኃብት መሆናቸውን ማረጋገጥ፥ ከትግላችን ዓላማዎች የመጀመሪያውን ቦታ ይይዛል። እነርሱ በማያሻማ መልኩ በኢትዮጵያ ሕዝብ እጅ ከገቡልን፥ የመራራው ትግላችን ዓላማ ተሳክቶልናል ማለት ብቻ ሳይሆን፥ የሰማዕታት ጓዶቻችንም ክቡር አፅም ዘለዓለማዊ ዕረፍትን ያገኝልናል ብለን እናምናለን። እኛ፥ ሥልጣን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው ስንል፥ ለመፈክር ማውለብለቢያና ለምርጫ ጊዜ የሚሆን አፍለኛ ቅስቀሳ ለመጠቀም አይደለም። ወይም ለፕሮፓጋንዳ ማደንቆሪያ፥ ለሕዝብ ቅስቀሳና ለፖሊቲካ ፍጆታ እንዲሆን ብለንም አይደለም። ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሕዝባችን ሥልጣነ-ማኅደር ውስጥ ከገቡልን፤ እራሱ ባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ የፈለገውን

የመንግሥት ሥርዓትም ሆነ የአስተዳደር አወቃቀር መክሮና መርምሮ ሊያበጅ ይችላል። መሪዎቹንም እንደ ፍላጎቱ መምረጥ መቻል አለበት። እስከዛሬ ድረስ መፍትሔ ያላገኙትንም ችግሮቹን በአሻውና በሚስማማው መልኩ እራሱ ይፈታቸዋል ብለን እናምናለን ። ይህንን የምንለውም በአጉል ተስፋ ሳይሆን፥ የሕዝባችንን ዕውቀት፤ ችሎታና ብልኀነት መሠረት በማድረግ ነው። ታዲያ ነፃና ርቱዕ ምርጫ ከዲሞክራሲ ሥርዓት ይመነጫል እንጅ፥ ወያኔ እንደሚቀባጥረው በተቃራኒው ሊሆን አይችልም። ያለ ሀገር ሕዝብ እንደማይኖር ሁሉ፥ ያለ ዴሞክራሲ ነፃና ርቱዕ ምርጫ ይገኛል ብሎ ማሰብ፥ቅዠት ወይም ተጨፈኑልኝና ለአታልላችሁ ማለት ነው የሚሆነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በበኩሉ ከእንግዲህ ወዲህ ሊታለል-ሊሞኝ የሚችል አይሆንም። የወያኔ መሪዎች የይስሙላ ምርጫ የሚያካሂዱት በሽፋንና በማጭበርበር ሥልጣን ላይ ተቀምጦ ሌላ ዙር ብዝበዛ ለማድረግ ነው። የማጭበርበሪያ ምርጫ የሚያካሂዱበትም ዘዴዎች በርካታ ናቸው። መሬትን በመንግሥት ቁጥጥር ስር አድርጎ አርሶ አደሩን ማስፈራራት፥ የማዳበሪያ ስርጭትን መቆጣጠር፥ በመሬት ሽግሽግ ስም አርሶ አደሩን መደለል፥በካድሬውና በገበሬ ማኀበር አባላት አማኻኝነት ገበሬውን ማስጨነቅ ወያኔ ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ጥቂቶቹ ናቸው። የወያኔ ምርጫ የተያያዘው አሁን ከሚያራምዱት የሰፈራ ዕቅድ ጋር ነው ብንልም ስህተት አይሆንም። በሚገባ ሳይጠና ፥ ምንም ዕቅድ በሌለውና ያለ ሕዝቡ መልካም ፍላጎትና ትብብር የሚደረገው አስገድዶ የማስፈር ርምጃ፥ ዓላማው ለሚቀጥለው የወያኔ ምርጫ፥ ሰፋሪዉን ሕዝብ እያስፈራሩ የምርጫ ካርድ ለማግኘት ነው። ሰፈራን ከምርጫ ጋር ማያያዝ ደግሞ በዘር ላይ ለተመሰረተ መንግሥት ይስማማዋል። አሁን በስፋት የተቀሰቀሰውን የተማሪዎች የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ጥያቄ፥ የ "ጎሳ" መልክ ያለው አስመስሎ ማቅረብ ፥ የወያኔ ርካሽ የዘር ፖሊቲካ ውጤት እንደመሆኑ፥ ሰፈራንም ለምርጫ መጠቀሚያ ለማድረግ የታቀደው መሰሪነት፥ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ችግሮች ያባብሳል እንጅ ፋይዳ አያመጣም። መቸም ከፅንሱ አሁን እስካለበት ደረጃ ድረስ ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብና በሀገራችን ላይ ያደረሰውን ጥፋት ማንም ኢትዮጵያዊ አልተረዳውም ብሎ ለመደምደም እንደማይቻል ሁሉ፥ አሁንም ወደፊትም የወያኔ መሪዎች ለኢትዮጵያ መልካም ያስባሉ የሚል አንድም ንፁህ ዜጋ አይኖርም።

ይህ በወያኔ መሪዎችና በእኛ መካከል ሊቀራረብ ቀርቶ፥ዓይን ለዓይን ሊተያይ የማይችለው ሌላው የምርጫ ልዩነት የመነጨው፥ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ከማየት ከመጣ መሠረታዊ ፍቅርና ጥቅም አኳያ ነው። የወያኔ መሪዎች ኢትዮጵያን የማይወዱ፥ ታሪኳን የማያውቁ፥ ሕዝቧን የሚንቁ፥ ለዜጎቿ ሰቆቃ የማይጨነቁ፥ ሀገሪቱን የሚያጠፉ ሲሆኑ፥ እኛ ደግሞ ሀገራችን ሞቷን ቀርቶ ሕመሟን የማንመኝ፥ ይህንንም በመሥዋዕት ያሳየ ፥ በመከራዋ ቀን ያልተለየ ት፥ ይህንንም በታሪክ ያስመዘገብን መሆናችን ነው ። ይህንንም አፋችንን ሞልተን ለመናገር የምንሻው፥ በትዕቢት በመወጠርና በውዳሴ-ከንቱነት ሳይሆን፥ ኢትዮጵያዊ ትኀትና በተላበሰ ባሕርይ በመስዋዕት ያስመዘገብነውን ዜና-መዋዕል ለማስታወስ ብቻ ነው ። ይህ በምንም ዓይነት ቢሆን ሊታረቅ የማይችል መሠረታዊ ልዩነት ታዲያ፥ በሕዝባዊ ምርጫ አመለካከት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖና አስተጋብዖ አስከትሏል ። ለእኛ፥ ኢትዮጵያ ሀገራችን ትላንትም ሆነ ዛሬ፥ ነገም ሆነ ዘለዓለም፥ ያው ሀገራችን ነች። በመከራ-በደስታዋ፥ በሀዘን በትካዜዋ፥ በድኀነቷም ይሁን በብልፅግናዋ፤ ያው እናት ሀገራችን ነች ። ቁርኝነታችንም የተያያዘው በርዕዮተ-ዓለም አኳያ፥ ወይም እንደማለዳ ጤዛ ታይቶ እንደሚረግፍ የአፍላ ጀብደኝነት ሳይሆን፥ ከዚያ በላይ ስፋትና ጥልቀት በአለው የአጥንትና የደም ትስስር ነው። ምርጫንም የምንመለከተው ከዚህ ለሀገራችን የረዥም ጊዜ ጥቅምና ለሕዝባችን ከአለን የጠለቀ ፍቅር አኳያ ነው። እንደዛሬዎቹ ኀጠኞች "ለእኛ ያልሆነች ኢትዮጵያ ትበጣጠስ" ከሚል አስተዛዛቢና አሳፋሪ መንስዔ የሚዘጋጅ ምርጫ፥ ውጤቱ ምን እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ በመሆኑ፥ ዝርዝርና ትንተና የሚያስፈልገው አይሆንም። የራስን አጀንዳ/ዕቅድና የግል ጥቅምን ለማራመድ ሲባል ብቻ፥ የተጭበረበረና ኢዴሞክራሲያዊ ምርጫ አካሄዶ የምርጫው አሸናፊ ሆኖ መውጣት፥ ምንም ሊያስገርምም ሆነ ሊያሳዝ አይችልም። ውጤቱን በቅድሚያ እንዲታወቅ ሆኖ የተሰናዳ የምርጫ ሂደት ፥ የወያኔን መሪዎች ሥልጣን ለማራዘም ሲባል ሕጋዊነት ያለው ለማስመሰል ቅብዓ- ሜሮን

ቢለቀልቁ፥ ሸንኩርት ባሕሪዪው ሆኖበት ይሸታል እንዲሉ፥ የወያኔን፥ ባሕርዩንና ተግባሩን አይለውጠውም ፡፡ ምርጫን በተመለከተ፥ በእኛና በወያኔ መካከል ያለው ልዩነት፥ መሠረታዊ-ዘለዓለማዊ - ስትራተጂያዊና ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፍ የሕዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ በቆመና፥ እንደ ዉሃ ፈሳሽ፥ እንደ ዕንግዳ ደራሽ ሆኖ ቶሎ ቶሎ ዘርፎ፥ ሀገር አጥፍቶ፥ ሕዝብ በታትኖ ሊኮበልል በወጠነ የዘረኞች ጥርቅሞ ቡድን መካከል ያለ ልዩነት ነው፡፡ ይህ ልዩነት ደግሞ ሰማይ ዝቅ- መሬት ከፍ ቢል ወይም በግል ምኞትና ጥቅም ፍለጋ ጨርሶ ሊጣብብ የሚችል አይደለም ፡፡ ይህ ግትርነት ከሆነ ቆመን መቅረቱን ፀጋ እንቀበለዋለን፡፡

ዛሬ ከሁሉ አስቀድሞ፥ ከማንምና ከምንም በላይ በአንገብጋቢ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የሀገራችን ኅልውናና የሕዝባችንም በአንድ ላይ አብሮ በእኩልነት የመኖር ጥያቄ ነው ፡፡ ለአያሌ ዘመናት አብሮ- ተባብሮ የ ረን የአንድን ሀገር ዜጋ፥ በብሄረሰብ ከፋፍሎ እንዲገነጣጠል ከሚፈቅድ የዘረኞች ሕገመንግሥት የሚመነጭ ምርጫ፥ ለሀገር-ለወገን ይጠቅማል ብሎ ማሰብ፥ ለአሁኑ ዜጋ ብቻ ሳይሆን፥ ለተተኪው ትውልድም ጊዜውን እየጠበቀ የሚፈነዳ ቦምብ እንደ መቅበር የሚቆጠር ነው፡፡ የወያኔን ምርጫ ተብዬ ሂደት እንዳለ መቀበል ማለትም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀስ በቀስ እየተበታተነ እንዲሄድ የሚያደረገውን የነወያኔን አደገኛ ዕቅድ ሕጋዊነት እንዲኖረው ማድረግ ይሆናል ፡፡ ይህ የዛሬው ትውልድ፥ ተተኪው ትውልድ እንዳይበታተን የተቻለውን ሁሉ ለማድረግ ከባድ ኃላፊነት እንዳለው ማስታወስ የሚያስፈልገን አይመስለንም ፡፡ ምክንያቱም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ለሀገሩ ኅልውና፥ ለዕምነቱና በእኩልነት ላይ ለተመረተ አንድነቱ፥ ከማንም የበለጠ ቀናዒ መሆኑን ደህና አድርገን ስለምናውቅ ነው፡፡በመሆኑም፥ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቅድሚያ ተልዕኮው፥ በዘርና በቋንቋ እየተሰነጣጠቀች በመሄድ ላይ ያለችውን ሀገሩን፥ ጠፍታ-ከመጥፋቷ በፊት ተረባርቦ ማዳን ነው፡፡ ይህንን አስቸኳይና አንገብጋቢ የሀገር ማዳን ግዳጅ፥ ሊተካው የሚችል ሌላ ብሔራዊ ጉዳይ አይኖርም፡፡ ሀገር፥ ሕዝብ፥ ነፃነት፥ ዲሞክራሲና ነፃ ምርጫ አንዱ ከሌላው ተገነጣጥለው የሚታዩ አይደሉም፡፡ ያው ሕዝቡም በብሔረሰብ እንዲከፋፈል ስለተፈረደበት፥ እነርሱም መከፋፋል አለባቸው ከአልተባለ በስተቀር! ሀገር አለን ካልን ሕዝብም መኖር አለበት፤ የሕዝብ መኖር ደግሞ ያለነፃነት ትርጉም አይኖረውም፡፡ ነፃነት አለን ካልን ደግሞ የዲሞክራሲ አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ ሊገባ የሚችል አይደለም፡፡ እነኝህ ዐበይት ጉዳዮች ማለት ሀገር፥ ሕዝብ ነፃነትና ዲሞክራሲ ተሟልተው ባልተገኙበት ሁኔታ፥ ነፃና ርቱዕ ምርጫ ይካሄዳል ብሎ ማሰብ አይቻልም ፡፡ አምባገነኑ ወያኔ በመሠረቱ ፀረ ዴሞክራሲና ፀረ ነፃ ምርጫ የሚሆነውም ለዚህ ነው፡፡

የወያኔ መሪዎች ሥልጣን ላይ ከተፈናጠጡ ጊዜ አንስተው፥ እንበለ-ኃፍረትና ይሉኝታ ኅልቆ-መሳፍርት የሌለው ቅሌትና ውሸት፥ ማጭበርበርና ማታለል እየፈፀሙና በዚህም ድርጊታቸው እየቀናቸውና እየተሳካላቸው መሄዱ፥ ሌላ ተጨማሪ ወንጀልና ጥፋት ለመፈፀም ገፋፍቷቸዋል፡፡ ለሚጠየቁት ኃላፊነት ሁሉ በተደጋጋሚ የሚሰጡት መልስ፥ ኑና ሞክሩን የሚል ሆኗል ፡፡ ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች እንደሚባለው፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ይህንን ያህል ንቀት የሚፈፅሙት፥ ትላንት ወደ ሥልጣን ያበቃቸውን የበላይ ጠባቂያቸውን በመተማመን ነው ፡፡ የጌታና የሎሌው ዝምድና ነገ እንዳልነበረ ሆኖ ሲንኮታኮት፥ ብሎም፥ ያ የማይቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የድል ጮራ ሲፈነጥቅ፥ አለቆቻቸው ሁሉ ፥ አጋልጠዋቸው እንደሚሄዱ ግን ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ታዲያ ዛሬ ላታቸውን ውጭ በማሳደር ቅሌት ውስጥ የገቡት የወያኔ መሪዎች፥ ነገ ኃፍረተ

ሥጋቸው ዕርቃኑን እንደሚቀር፥ ሀገራቸውን በመክዳትና ሕዝባቸውን በመበደል፥ ለውጭ ኃይል ሲሰግዱ የነበሩ መሪዎች የመጨረሻ አወዳደቃቸቸው ጎያው ምስክር ነው ። ይህንን የታሪክ ሐቅ አስመልክቶ፥ ብዙ ምዕራፍ ሳንሄድ፥ የኢራኑን ሻህ ባኃላቪ፥ የሩማንያውን ኒኮላይ ሻውቼስኮ፥ የዛይሩን ሞቡቱ፤ የጆርጂያውን ሸቨርናዘንና የራሳችንንም የጓዳ ጨቋኞች ዕጣ ፈንታ ወይም የመጨረሻ አወዳደቅ መጥቀሱ ይበቃል። የውጭ ኃይሎች ደግሞ የዛሬ ሎሌያቸውን ነገ በሚያስገርም ፍጥነት ለመክዳት ዞሮ የሚያይ አንገት አልተፈጠረላቸውም። የዓለም ዲፕሎማሲ የሚያጠነጥነውም ሁሉ ጊዜ በቋሚ ጥቅም ዙሪያ ላይ ብቻ ነውና። የጥቅም ጉዳይ ከተነሳ ደግሞ፥ እንኳንስ እንደ ኢትዮጵያ ያለ ፉት ሲሉት ጭልጥ የሚል ኢኮኖሚ ላለው ሀገር መሪ ሊጨነቁ ቀርቶ፥ የደለበ የነዳጅ ምርት ያላት ኢራንንም ገብሮላቸው ለነበረው ሻህ ጎን በመቆም ከሕዝባዊ ቁጣ ማዕበል አላስጣሉትም።

መሠረታዊ ዕምነቱን፥ ዓላማውንና ራዕዩን በሕዝብ ፍቅር ፥ ዕምነትና አክብሮት ላይ መሥርቶ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም ድርጅት፥ ከሁሉም በፊት ኃላፊነቱና ተጠያቂነቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ መሆን እንዳለበት የሚያከራክር ጉዳይ አይሆንም። ሕዝብ በሚባልበት ጊዜ ሁሉ በግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው በርካታ መሠረታዊ ጉዳዮች ይኖራሉ። የሕዝብ ትርጉም በጥሬ ቃሉ ብቻ የሚታይ ሊሆን አይችልም። ሕዝብ ስንል፥ ታሪኩን፥ ባኅሉን ጠባዩን፥ ዕምነቱን፥ መስተጋብሩንና ሥነልቦናውን እንዲሁም የወደፊት ተስፋውንም ያካትታል። ታዲያ የሀገራችንን ቸግር መፍታት አለበን ብለን መታገል ካለብን፥ የችግሮቹ አፈታትና መፍትሔያቸው የሚሽከረከሩት ከላይ በተዘረዘሩት ሁለንተናዊ አመለካካት ዙሪያ መሆኑን ልንስተው አይገባንም። መሠረታዊ ጉዳዮቹን ከዚህ አኳያ ስንመለከታቸውና ምንም ጊዜም ቢሆን የሀገራችን ውስብስብና ስር የሰደዱ ችግሮቻችን ለመፍታት ስንጥር፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ልክ እንደማንኛውም የዓለም ሕዝቦች የራሱ-የግሉ የሆነ ባህል፥ የቆየ ልምድና የደለበ የሕይወት ተመክሮ ባለፀጋ መሆኑን ሳንዘነጋ መሆን አለበት። ሕዝባችን ከጥንቱ-ከጧቱ የራሱን ችግር የሚፈታበት ልዩ ባሕሪይ እንደነበረውም በማመንም ጭምር ነው። የምርጫን ሁኔታ ስንመለከትም ከዚህ ዕይታ ነጥለን አይደለም። ምንም እንኳን ባህላዊው ሕዝብ፥ ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደርና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ኖሮት፥ ምርጫን ያካሄድ ነበር ባይባልም፥ ከቆየው ባህል፥ ታሪክና የአሠራር ልምድ በመነሳት፥ የማንንም መመሪያና ተፅዕኖ ሳይቀበል፥ በራሱ አነሳሽነት የሚያምነውን የሚጠቅመውንና የሚያከብረውን ሰው በየአካባቢው፥ የደብር/የጎበዝ አለቃውን፥ የአርበኛ መሪውን፥ቆሮውን፥ የሽማግሌ ሽንጎውን፥ ብሶቱንና ይግባኙን ለባለሥልጣኖች የሚወስድለትን መልዕክተኛና የመሳሰሉትን በየጊዜው የመምረጥ፥ የመቆጣጠርና የማውረድ ሥልጣንና ልምድ ነበረው። ይህ የቆየ ባህላዊ የአሰራር ልምድ እንከን የሌለበት ነበር ለማለት ባይቻልም፥ ሌላው ቢቀር ሕዝቡ ቢያንስ፥ ያለማንም ተፅዕኖና ያላንዳች አስገዳጅ የራሱን ነፃ ምርጫ ያካሂድ ነበር ለማለት የሚቻል ይመስለናል።

ከቅርብ ዘመን ወዲህ የመጡ ማዕከላዊ መንግሥታት፥ የየራሳቸውን ፈላጭ-ቆራጭ አገዛዝ በመመስረት፥ የሕዝቡን የቆየ ባህላዊ አሠራርና ልምድ በማጥፋት፥ በአምባገነን ሥርዓት ተኩበት። ሕዝቡም " ከሁለት ያጣ ጎመን" ሆኖ ቀረ። የአያሌ ዘመናት ታሪክና የበለፀገ ባህል የነበረውን ሕዝብ፥ ከቆየው ባህሉ ላይ በመመርኮዝ የዴሞክራሲያዊ ምርጫ የማካሄድ ዕድል የሚነፈግበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም። ሌላው ቢቀር፥ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ፍፃሜ በኋላ በዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ እንደ ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ሚና ስትጫወት ከነበረችው ከሕንድ ጋር የሚመሳሰል የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሀገራችን ልትጎናፀፍ በተገባት ነበር። ሕንድ፥ ባህሏን፥ ታሪኳንና የዜጎቿንም ዕምነት ጠበቃ ተሟላ ባይባልም መሠረት ባለው ዴሞክራሲ ሥርዓት የምትደተዳደር ሀገር መሆኗ ለአብነት የሚጠቀስ ነው።

ምርጫን አስመልክቶ ለሕዝባችን የነበረን፥ ያለንና የሚኖረን ራዕይ፥ ለሀገራችን ከምናልምላት ስትራተጂያዊ ዓላማ፥ ዘላቂ ጥቅምና ዘለዓለማዊ ሰላም ጋር የተቆራኘ እንጅ፥

በአንድ የምርጫ ወራት ላይ በማተኮር፥ በሆነው መንገድ ሥልጣንን በሸርፍ ወይም በፍርፋሪ ደረጃ አግኝቶ “እንደ ተመኘኋት ይኸው አገኘኋት” የሚል ወያኔያዊ ዳንኪራ ለመደንከር አይደለም። የዚህ ዓይነቱ ድፍረትና ቅሌት የነመለስ ዜናዊ እንጅ፥ እኛን ሲያልፍም የሚነካን ሊሆን አይችልም። ርቱዕና ነፃ ምርጫ ሊመጣ የሚችለው ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአጽናፍ እስከ-አጽናፍ ገደብ የለሽ ዴሞክራሲያዊ መብቱን ሲጎናፀፍ እንጅ፥ እኔ ብቻ አውቅልሃላሁ፤ ይህንን ምረጥ፥ ያንን አትምረጥ፤ በዚህ ጊዜ ምረጥ፥ ወዘተ.. በሚል መመሪያና ተፅዕኖ በላዩ ላይ እየተሾጎደጎደበት በአባለበት ሁኔታ ሊሆን አይችልም። እንደ-እንጀራ እናት ንፍገት፥ በቁንጣ - ቁንጢ የሚሰጥ መብት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ክብርና ታሪክ ጋር የሚሄድ አይደለም። ኸረ ለመሆኑ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይነታውን ማን ወስዶበት ነው ፍርፋሪ የሚጣልለት? ከወያኔ ጋር ያለንን የሰማይና የምድር ያህል የተራራቀ የምርጫ ግንዛቤ ልዩነት ወደፊት የምናሳየው፥ በተግባር አፈፃፀም እንጅ በወረቀት ላይ በሰፈረ አገላለጽ አለመሆኑ ግልፅ ነው። በሕዝብና በሀገር ላይ አምባገነናዊ ሥርዓትን ያስፈነው ወያኔ የባለይነቱን ይዞና የሚያመቸውን ሕግና ደምብ አውጥቶ ፤ሕዝብን አፋኝና አስፈራሪ ኃይሉን መዋቅሩን ዘርግቶ፤ ሀቀኛ ተቃዋሚችን አዋክቦና አግልሎ፤ ልምረጥ በነፃ ያለውን እየቀላ በሚያካሂደው ወያኔያዊ ቧልት አለመሳተፍ፥ የዜጎች መብት ብቻ ሳይሆን፥ ግዴታም ነው። ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ስንል፥ ከወያኔ ቁጥጥር ነፃ የሆነ፤የሕዝብን መብት ያሰከበረና ውጤቱም ተከባሪ የሚሆን ሁሉን ድርጅቶች የሚያሳትፍ ሃቀኛ ምርጫ ማለታችን ነው። የወያኔ የብቻ ሩጨና ድል ከዚህ በፊትም ታይቶ ከራሱ ውጪ ማንንም አላረካም። ይህንን ውንብድና እንደገና ዘንድሮም ድገመው ያለም ሕዝብ ስለሌለ፥ ወያኔ ሀገርና ዓለምን አታልላለሁ ብሎ ምርጫ ሲል፥ ወግድ! ብሎ ማሳፈር እንጂ፥ ጆሮ ሊሰጠው አይገባም። የነፃ ምርጫ መስፈርቶችን መቀበልም፥ አይቀሬ ሽንፈቱን መቀበል ነውና ይህን ዓይነት ብልኀነት ወይም ሕዝብን አክባሪነት፥ ከዋልጌዎቹ ጥርቅም የሚጠበቅ አይደለም። ይህም የሚያረጋግጠው፥ ወጣም ወረደም ነፃ ምርጫን በሀገራችን ዕውን ለማድረግ፥ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ያመረረና የተባባረ ፀረ ወያኔ ትግል ማፋፋም ግዴታችን መሆኑን ነው።